ፓኖራማ ቁጥር 70

የትዝብት አድማስ

ግንቦት 9 ቀን 2001 ዓም

<u>አምባገነን ፍርሀትን ፥ ፍርሃት ውሸትን ይ¨ልዳል</u>

ማነኛውምሥርዓት/መንግሥት ከሚያስተዳድረው ሕዝብ ጋር ሊኖረው የሚገባው ግንኙነትና ስምምነት፥ በህግ ከልተደነገገና ካልተገደበ፥አውራ-ዘለልነት መስፈን እንደሚችል ሳይታለም የተፈታ ነው ። አውራ-ዘለልነት እየቆየ እየሰፋና ገደብንም እየተላለፈ በሄደ ቁጥር ደግሞ ፥ሕዝቡ ወሰንህን አልፈህ ገፍተኸኛል ብሎ ይቆጣል፥ ያጎረመርማል፥ ልዕልናውንና መብቱን ለማስከበርም ይነሳል ። ያምፃል ። ሥርዓቱም የሕዝቡን ቁጣ ስለሚፈራና ኅልውናውን ለመጠበቅ ወደ ኃይልና ህገ-ወጥ ተግባር ያዘነብላል ። በገዥና በተገዥ መካከል ሊኖር የሚገባው ሕጋዊና መልካም ግንኙነት እየደፈረሰ ከሄደ፥ ሕግና ሥነሥርዓት እየቀሩ አመጽና ፍጥጫ ይነግሳሉ ። መንግሥትም የሕዝቡን ቆጣ እንደ እሳተ-ገሞራ ይፈራዋል ። የሕዝብ ቁጣ እየጨመረና ኃይሉ እየዳበረ በሄደ ቁጥር ደግሞ፥ አመፁ እንደ ቋያ እሳት እየተቀጣጠለ ሀገር-ምድሩን ያዳርሰዋል። የአገዛዙም አምባገነንነት ፈጦ ይወጣል። በጠራራ ፀሀይ ሕዝብ ይገድላል፥ያለርኅራኄ የጅምላ ጭፍጨፋ ያካሂዳል ። የአምባገነንነቱን ባኅርይ በነባቢት ሳይሆን በድርጊት ያስመሰክራል። " ተው በሉት ይህን ሕዝብ መካር የለውም ወይ፥ ምላጭ ከተሳበ (ማ) አረር አይደለም ወይ። " እያለ የቆቀ የባጡን ያስገጥማል ። መካሪ መስሎ ያስፈራራል ። ፍርሃቱን የሚቀንስለት እየመሰለው ! ፍርሃት ገደቡን ካለፈ ደግሞ ፈሪው የማመዛዘን ችሎታውን ያጣል ። ሀሰቱን በፍርሃቱ እየለወሰ ጭካኔውን በጭንቀቱ እያጣጣመ ዕድሜውን ለመቀጠል ይፍጨረጨራል ። ከማይቀረው የምልዓተ- ሕዝብ ቁጣና ቅጣት የሚያድነው እየመሰለው !

የኢትዮጵያ ሕዝብ በቅርብ ታሪኩ የሦስት አምባገነኖች ሰለባ በመሆኑ ፥ የአምባገነኖችን ባኅርይ ፥ ይዘትና ድርጊት፥ ፍርሀትና ውሸት በሚገባ ያውቀዋል ። "ትሻልን ሰድጄ ትብስን አመጣሁ" እያለ የዕፎይታ መፅናናትን ፥ የመቆያ መረጋጋትን እያስተናገደ ከመታዘብ በስተቀር፥ በሦስቱም አምባገነኖች የቅርፅ እንጅ የይዘት ልዩነት እምብዛም አያይባቸውም ። የሦስቱም ሥርዓቶች የአምባገነን ባኅሪዎችና ድርጊታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ፥ የወያኔ መሪዎች ለአምባገነን አገዛዛቸው ሊጠቅማቸው የቻለውን መሠረታዊ ተመክሮዎች ከአፄው ሥርዓትና ከደርግ አገዛዝ በሚገባ ቀድተው ይጠቀሙበታል ።<u>" ሀበሻን ፊት ሳታሳይ ኃይል</u>

እየተጠቀምክ ግዛው ” የሚለውን የድርግን የአገዛዝ ስልትና ሆኖ መገኘት ሳይሆን ፥ መስሎ መታየት የሚለውን የአፄውን ዘዴ ፥ እንደ ቋሚ መመሪያቸው አድርገው ይጠቀሙበታል ። የወያኔ መሪዎች በማነኛው መስፈርት ሲመዘኑ የመላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለማይወክሉ ሁልጊዜ ጎዳጣን መሆናቸውን በሚገባ ይረዱታል ። በኢትዮጵያና በዜጎቿ ላይ ታሪክ የማይረሳው ብሔራዊ ወንጀል መፈፀማቸውንም ማንም ሳያመለክታቸው እነርሱ ራሳቸው አሳምረው የሚያውቁ ቡድኖች ናቸው ። በመሆኑም ፥ ተወድደውና ተከብረው መኖር ሳይሆን ፥ ተንቀውና ተጠልቶ መኖር ብቻ ያዋጣናል በሚል ሥነ አዕምሮ ጭጋግ ውስጥ ተሸብበው በፍርሀት ውስጥ ይኖራሉ። በዚህ ዓይነት የሥነ-አዕምሮ ሂደት ለመራመድ ደግሞ የግድ እየዋሹና እራስን እያታለሉ የመኖር ችሎታን ይጠይቃል። ራስን እያታለሉ የመኖር ችሎታ ደግሞ መሠረቱ ውሸት ነው ። ለመኖር ብቻ ሲሉ መኖር ፥ በሥልጣን ለመቆየት ብቻ ሲባል መቅጠፍ ፥ የሌላውን ተቀባይነት ለማግኘት ሲባል እየዋሹ የዒላማቸው ሰለባ ያደረጉትን ክፍል ማስጠላት ፥ ማጣላት ፥ ማጋጨት የተቃዋሚውን ማንነት ጥላሸት መቀባት ፥ ዕውነትና ንጋት እያደር ይፈጋል የሚለውን ሀቅ አለመቀበል ሁሉ ሲደመር ዞሮ ዞሮ ምንጩ ፍርሀትና ውሸት ነው ። ሁሉም ዜሮ ዜሮ፥ ባዶ የፈረስ ምግብ ፋርሽካ ፥ ቢከፍቱት ተልባ ፥ የጧት ጤዛ ነው። የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ችግር በተለያየ መልኩ እነርሱ እንዳላመጡት ሁሉ፥ ወደ ተቃዋሚ ድርጅቶች ሲያላክኩ መፍጨርጨራቸው ሊያስገርም ከቶ አይችልም ።

በተለያዩ ጊዜያት አዳዲስ የመዋሸት ዘዴ መጠቅም፥ በየወቅቱ የሚገጥማቸውን ውጥረትና የሚከሰትባቸውን የውስጥ ችግር ለጊዜውም ቢሆን በሥልጣን ሊያቆየን የሚችል ጊዜ ይሰጠናል ብለው ራሳቸውን ያታልላሉ። “አገመገመ ሰኔና ግንቦት ያለው ሊበላ የሌለው ሊሞት። ” እንዲሉ፥ የግንቦት ወር በየዓመቱ ሲመጣ ከመንግሥት ግልበጣ ጋር የተየያዘ ምትኃት ያለው ለማስመስል ይሞከራል ። የሀገራችን ስር የሰደደ ችግር ግን በዘመናት የተጠራቀመ የአምባገነን ጭቆና ድምር ውጤት እንጅ መስከረም ሲጠባ የመጣ ፥ ኅዳር ሲታጠን የተከሰተ፥ እንደ ግንቦት ልደታ በምቸት የተቀቀለ ንፍሮ ይደለም ። አብዛኛዎቹ አምባገነኖች፥ ኮኮብ ቆጣሪዎች ፥ ጋኔል ሳቢዎች ፥ ባዕዳን አምላኬዎች ፥ ምትኃት አማኞች፥ ሞራ ገላጭዎች፥ጠንቋይ ቀላቢዎች፥ የቡና ፊንጃል ደፊዎች፥ ጨሌ መችዎችን ሁሉ በዙሪያቸው መኮልኮል፥ ለሥልጣን መቆያቸው ይረዳናል ብለው ያስባሉ ። ወረኃ ግንቦት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ለውጥ ሊያስመጣ የሚችል ክስተት ሊፈጥር ይችላል ብለው ይሰጋሉ ። ለዚህም የታሪክን አጋጣሚ ለማጠየቂያ ይጠቅሳሉ ። በ1928 ዓም የኢጣሊያ ወራሪ ጦር ሰኔና ግንቦት አዲስ አበባ መግባቱን እንደ ማስረጃ ያስታውሳሉ ። በግንቦት ወር በደርግ መኮንኖች የተሞከረውን መፈንቅለ-መንግሥት ይዘክራሉ ። የወያኔዎቹ የግንቦት አካባቢ የመፈንቅለ-መንግሥት አስቂኝ ድራማና ከዚያ በኋላም

የታዩት የመለስ ዜናዊና የበረከት ስምዖን የመገለባበጥ የቲያትር ጨዋታ÷ ውስጥ ውስጡን እየተብላላ የመጣውን የውስጥ ችግራቸውን አስቀድሞ ለማስተንፈስና የሚያሰጓቸውን ቡድኖች ለመምታትና ለማጥፋት ተጠቅመውበታል ። ለሚቀጥለው ዓመት የወያኔን ምርጫ እነርሱ በሚፈልጉት መንገድና ሂደት ለመጥረግ እንዲያመቻቸው ለማረጋገጥ ከአሁኑ የሚያሰጓቸውን ለማስወገድ እንዲችሉ መልካም አጋጣሚ የሆነላቸው የግንቦቱን መፈንቅለ-መንግሥት ድራማ እየተጠቀሙበት ነው።መንግሥቱ ኃይለማርያም ለሀገር መከላከያ የጀርባ አጥንት ነበሩ የሚባልላቸውን ጄኔራል መኮንኖች እንዳጠፋቸውና በጭካኔና በአሳፋሪ ድርጊቱ ሀገሪቱን አንገት የሚያስደፋ የአረመኔ ተግባር እንደፈፀመ ሁሉ ÷ የዛሬዎቹም ባለተረኞች የድራማ ልብሳቸውን ብቻ በመቀየር ተመሳሳይ ቲያትር በማሳያት ላይ ናቸው ። መለስ ዜናዊ÷ሊገሉኝ ሲሉ እጅ-ከፍንጅ ያዝኳቸው ያላቸውን ጄኔራሎችና ሌሎች ሲቪሎች ለዕርድ ጭዳ እያዘጋጃቸው እንደሆነ ይፋ አድርጓል ። " ለሚቀጥለው ዓመት የሚያብድ ዘንድሮ ጨርቁን መቅደድ ይጀመራል።" እንዲሉ÷የወያኔ ሰዎችም እንደ ድመት የራሳቸውን ሰዎች እየቀረጠፉ በመብላት ናቸው።

ይህ የፈንቅለ- መንግሥት ጉዳይ ከተነሳ ÷ ሙከራው በሀገራችን እንደማይሳካ ያለፉት ተመክሮዎች ያረጋግጣሉ። የሀገራችንን የፖለቲካ ሂደትና ሁኔታ በቅርብ የሚከታተሉ ታሪክ መዝጋቢዎች እንደሚያስረዱት÷ ከ1953ቱ የታህሣሱ ሙከራ በኋላና እስከ 1966 ቱ ዓ/ም ሕዝባዊ አመፅ ድረስ ማለትም በአስራ ሦስት ዓመታት ውስጥ÷ ቢያንስ አስራ ሳባት ሙከራዎች ተደርገው ሁሉም በእንጭጫቸው እንደተጨናገፉ ይገመታል ።ሁሉም የከሸፉት ÷ከጠንሳሾቹ አንዱ ወይም ሌላው ከሃዲ÷ምሥጢር እያወጣ ሌሎቹን ስለሚያጋልጥ ብቻ ነበር። ለነኝህ የታሪክ ጠባሳ ክስቶችና ለታሪክም ግንዛቤ እንዲሆን ÷ በወቅቱ ሕዝቡ በስፋት የሚያውቃቸውን ሁለት የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎችን ጠቅሰን አናልፋለን። አንደኛው እነ ኮሎኔል ዕምሩ ወንዴና ኮሎኔል አስናቀ ዕንግዳ የነበሩበት ሙከራ ነበር ። ይህ ሙከራ አብሯቸው በነበረ አንድ ከሃዲ አማካኝነት ምሥጢሩ ስለተጋለጠ ÷ ጠንሳሾቹ ለዕስርና ለመከራ ተዳርገዋል። ሁለተኛው የአፄውን መንግሥት ለመገልበጥ የተደረገው ሙከራ በታወቁት አርበኛ በደጃዝማች ታከለ ወለደ ሐዋርያት የተሞከረው ነበር። ይህም እንደዚሁ በምክሩ ውስጥ በነበሩ ከሃዲያን አማካኝነት ምሥጢሩ ለንጉሡ ስለተነገራቸው ከሽፏል። ስም-ጥሩው አርበኛና ጀግና ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያትም እጄን አልስጥም በማለት ተታኩሰው ለመሞት በቅተዋል ። በአሁኑ ወቅት አስፈላጊ ሆኖ ስላላገኘነው ÷ የከሃዲውችን ስምና ማንንት ከመመዝገብ ተቆጥበናል።ብቻ አንድ ቆም ነገር አስምሮ ለማለፍ እንፈልጋለን ይኸውም÷ <u>" መፈንቅለ- መንግሥት ለመጠንሰስ ከማሰብህ በፊት÷ አስቀድመህ በየአንዳንዱ 12÷ ሐዋርያት ( ጠንሳሾች) ውስጥ አንድ አንድ ይሁዳ ሊኖር እንደሚችል አትዘንጋ ። " የሚለውን ነው።</u>

አስመራ ላይ የተጠነሰሰው የግንቦቱ የደርግ ጄኔራሎች ሙከራ በ1000 ኪሎ ሜትር ርቀት አዲስ አበባ ላይ ሊሳካ ያልቻለ፥ የዘንድሮው ግንቦት ተሞከረ የተበላው፥ አሜሪካ ተጠንስሶ በሪሞት ኮንትሮ አዲስ አበባ ይሳካል ብሎ ማሰብ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደገና እናሞኝህ እንደ ማለት ነው :: አምባገነኖች እየደከሙ ፥ እየተጠሉ ፥ ሕዝቡንም በይበልጥ እየፈሩት በመጡ ቁጥር ፥ እየተደናገጡ መሄዳቸው ገሀድ ነው :: ፍርሃታቸውን በውሸት እየለወሱ አስቂኝ ቲያትር መስራት፥ የዕድሜያቸው መቀጠያ ዘዴ እየመሰላቸው ! ይህን የታዘበው የአዲስ አበባ ሕዝብ ሰሞኑን በሚከተለው ስንኝ ሊገልፃቸው የፈለገውም ወዶ አይደለም::

*ወያኔና ውሸት፥ መለስና ፍርሀት ምንና ምን ናቸው፥*
*የጆሮ ጉትቻ ያንገት ድሪ ናችው፥*
*ጉትቻው መሳቂያ ድሪው ማነቂያቸው::*

ወጣም ወረደም ፥ መሠረታዊ ለውጥ ሕዝብን ባቀፈ ትግልና እንቅስቃሴ መሆኑ ለውጤቱ ስኬት አስፈላጊ ነው :: ለውጥ የጥቂቶችና የምርጦች ጥረትና ምኞት ሳይሆን፥ የምልዓተ-ህዝቡ መራራ ትግል ውጤት መሆን አለበት::